# አስቸኳይ መልእክት ኢትዮጵያ ውስጥ ለምትኖሩ ሁሉ!!

ምሕረት ዘገዬ

ይህን አስቸኳይ መልእክት ለመጻፍ ያነሳሳኝ ትናንት አመሻሽ ላይ ልገዛ የጠየቅሁት አንድ ተሽከርካሪ ዋጋው እጅግ አስደንጋጭ ሆኖ በማግኘቴ ነው፡፡ ይህ የሰሞኑ የዋጋ መናር አንድ ብቸኛ መልእክት አለው፡፡ ይህም መልእክት ወያኔዎች በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በዶ/ር አቢይ አህመድ ላይ የአሻጥር (sabotage) ዘመቻ መክፈታቸውንና አጠናክረው መቀጠላቸውን የሚጠቁምና ለሀገራችን ከፍተኛ የደኅንነት ሥጋትን የደቀነ ሕወሓታዊ መልእክት ነው፡፡

በግልጽ የሚስተዋለው ችግር የዋጋ መናር ብቻም አይደለም፡፡ የመንግሥትን የአገልግሎት ተቋማት በኃላፊነትና በሠራተኝነት የያዙት በአብዛኛው እነሱው በመሆናቸው - ያደባባይ ምሥጢር እኮ ነው - በማኅበረሰቡ ላይ እየደረሰ ያለው ስቃይ ፈርጀ ብዙ ነው፡፡ ለአብነት በብዙ ቦታዎች ውኃ የለም - እንደፈለጉ ይዘጉታል ወይም ያቋርጡታል፡፡ መብራትም በተደጋጋሚ ይጠፋል፡፡ የሚጠየቅ የለም፡፡ መንገዶችን እዚህም እዚያም መቆፈር ነው፤ በውጤቱም በየቦታው በሚፈጠር የትራክ ጭንንቅ አንድ ቦታ ላይ ተገትሮ መዋ ነው፡፡ ሠራተኛ በሰዓቱ አይገባም፡፡ አዲስ አበባን ከቀኑ አራትና አምስት ሰዓት ላይ እንዲያ ተጨናንቃ ለሚያይ የውጪ ታዛቢ በሀገሪቱ ሥራ መቼ እንደሚሠራ ለማወቅ መጓጓቱ አይቀርም፡፡ ሰዎች በመኪና መጓዛቸውን ልክ እንደሥራ ሳይቆጥሩት አልቀረም፡፡ ብቻ ሌሊት እንኳ እንጂ ቀን ቀን በዓላትን ጨምሮ የመንገድ ጭንቅንቁና የመኪና አደጋው እጅግ አሳሳቢ እየሆነ ነው፡፡ በዚህ ላይ እሳት ቢነሳ እንዴት እንደሚጠፋ፣ ጣር ላይ ያለ በሽተኛ በአምቡላንስ ወደ ሐኪም ቤት ሄዶ እንዴት እንደሚታከም፣ ፖሊስ ተልኮ የሚገዳደሉ ሰዎችን እንዴት እንደሚያስቆም… አስቡት፡፡ ለአሥር ደቂቃ መንገድ ሰዓታትን መፍጀት እየተለመደ ነው፡፡ በዚህ መሀል ነው እንግዲህ ሀገር አድጋለች እየተባለ የሚደሰኮርልን፡፡ ኢንተርኔት ይቆራረጣል ወይም አንድያውን ይዘጋል፡፡ ጠያቂም ተጠያቂም የለም፡፡ ወደ ቢሮዎች ሲኬድ ሠራተኛ የለም - "ዓመት ፈቃድ ላይ ነው/ናት ወይም ስብሰባ ላይ ነው//ናት" ይባልልህና ሰው እንዲጉላላ ይደረጋል፡፡ ይሄ ሁሉ የአሻጥሩ አካል ነው ወይም የወያኔው አገዛዝ የዓመታት የልፋት ውጤት ነው፡፡ ተነግረው በማያልቁ ችግሮች ተተብትበናል፡፡ ለነዚህ ሁሉ ችግሮች አንድ አቢይ ብቻ ሣይሆን ሺዎች አቢዮች ያስፈልጉናል፡፡ ያገኘነውን አቢይ ግን እንደዐይናችን ብሌን እንጠብቀው፡፡ አንድ ዐይና በአፈር አይጫወትምና፡፡ እንዲህ የምለው የሻጥሩን ክረት ስታዘብ ሰዎቹ እንዲህ የጨከኑበት አንዳች ነገር ቢሸታቸው ነውና "ግዴለም፤ ይህ ወጣት ሰው ሳይጠቅመን አይቀርምና ጊዜ ሰጥተን እንየው" ከሚል በጎ አስተሳሰብ ተነስቼ ነው፡፡ አይበልብኝ እንጂ ብሳሳት ለመታረም ዝግጁ ነኝ፡፡

አሻጥር መሥራት አንድን መንግሥት ከሥር መሠረቱ ሊያናጋና ቀስ በቀስ ገዝግዞ ሊጥለውም ይችላል፡፡ ይህን ዘዴ ወያኔዎች የተካኑበት ስለሆነ በሚገባ እንደሚጠቀሙበት እሙን ነው፡፡ ካለፉት 27 ዓመታት ወዲህ የሕወሓት አባላት ያልተቆጣጠሩት ነገር የለም - ሀብትና ንብረታችንን ይቅርና ነፍስና ሥጋችንን ጭምር በወለድ አገድ ይዘው እንዳሻቸው እያደረጉን ናቸው፡፡ ዶ/ር አቢይ ደግሞ ከኢትዮጵያ አምላክና ከድሃ ሕዝቧ በስተቀር ምንም የሚመካበትም ሆነ የሚኮራበት ነገር የለውም፡፡ ስለዚህ ምን እናድርግ? ማድረግ የምንችለው ነገር ሞልቷል፡፡ ወደዚያ እመጣለሁ፡፡

ትናንት የጠየቅሁት መኪና ከስድስት ወራት በፊት ከቦታው ከ180 እስከ 200 ሺህ ብር ይሸጥ እንደነበር አውቃለሁ፡፡ ትናንት እቦታው ድረስ ሄጄ ስጠይቅ ግን የመጨረሻ መሸጫ ዋጋው 300 ሺህ ብር እንደሆነ ተነገረኝ፡፡ በስድስት ወራት ውስጥ ከ120 እስከ 100 ሺህ ብር ጨምሯል፡፡ የሀገራችንን የዋጋ መናር ብረዳም የሰሞኑ ግን እጅግ ለዬት ይላልና - ይህም ክስተት አለነገር አልሆነምና - ልንጠነቀቅ እንደሚገባን በዚህች አጭር ማስታወሻ ለማሳሰብ ፈለግሁ፡፡ ምክንያቱን ስጠይቅ የዶላር ምንዛሪ በመጨመሩ እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ ዋና ምክንያቱ ግን የወያኔ አሻጥር እንደሆነ መረዳት አይከብድም፡፡ ከዶላር ጋር የማይገናኙ የምግብና የመጠጥ ሸቀጦች እንዲሁም አልባሳትና የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ ከነበረው ዕጥፍ ድርብ ሆነዋል፡፡ የምንሰማው የዋጋ መጠን ሁሉ ከኃይለ ሥላሴና ከደርግ ዘመን ይቅርና ከጥቂት ወራትና ሣምንታት በፊት ከነበረው ዋጋ እንኳን ፈጽሞ የሚራራቅ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ነገር ሕወሓት ሠራሽ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡

ለጤፍ ምን ዶላር ያስፈልጋል? ለቲማቲም ምን ዶላር ያስፈልጋል? ለሽንኩርት፣ ለጨው፣ ለሚጥሚጣ፣… ምን ዶላር ያስፈልጋል?....

ሳታመካኝ ብላኝ ነው ነገሩ፡፡ "ባሏን የጎዳች መስሏት…" እንዳንል ከሞላ ጎደል ሁሉም ወያኔ ትግሬዎች በሰሞነኛው ችግር አይጎዱም፡፡ ሁሉ በጃቸው ሁሉ በደጃቸው ስለሆነ የሚጎዳው ጭቁኑና ሌላው ሕዝብ ነው፡፡ እነሱ ዘንድ ውፍረት እንጂ ዕጥረት የለም፡፡ ይህንንም ስል እንደብዙኃኑ እየተቸገረ የሚኖር ትግሬ የለም ለማለት አይደለም፤ ብዙ አሉ፡፡ ለወንበሩና ለከረፋው ዘረኛ የአፓርታይድ ሥርዓት ቀረቤታ ያለው ትግሬም ይሁን ጉሙዝ፣ አደሬም ይሁን ጊሚራ ግን የዕቃዎችና የሸቀጦች ዋጋ  የሰማይን ጣርያ አልፎ ቢነጉድ ቅንጣት ታህል አይቸገርም፡፡ አንዳንድ ወያኔ እኮ በልጁ የልደት በዓል ሽራን ውስጥ ደግሶ በብዙ ሚሊዮን የሚገዛ ስጦታ ለባለቤቱና ለባለልደት ልጁ የሚያበረክትና ገንዘቡን የት ወስዶ እንደሚጥለው የሚቸገር ነው፡፡ ስለዚህ ጤፍ ሦስት ሺህ ገባ አሥር ሺህ፣ ቤንዚን ሃያ ብር ገባ መቶ ብር፣ አንድ ቁምጣ ከሰል አምስት መቶ ብር ገባ ሺ ብር ደንታው አይደለም፡፡ ልዩነታችን እኮ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው፡፡ አይበለውና - ኧረ ከፈለገስ ይበለው ምን አገባኝ - አይበለውና አንድ ነገር ቢነሳ የት ሄደው እንደሚኖሩ ፈጣሪ ይወቀው፡፡

እነዚህ ወያኔዎች ልክ እንደ አህያዋ እኔ "ከሞትኩ ኢትዮጵያ ድራሽዋ ይጥፋ!" ብለው ስለማሉ ምንም ዓይነት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ቢፈጠር ደስታቸው እንጂ አንዳችም የሚያሳስባቸው ነገር የለም፡፡ **ስለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት ሰው ሠራሽ የገበያ ግርግር እየፈጠሩ ሕዝቡ እንዲማረርና ዶ/ር አቢይም እንዲጠላ ባለ በሌለ ኃይላቸው እየተወራጩ የሚገኙት**፡፡ ወያኔዎች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማማውን እስከተቆጣጠሩ ድረስ - ልብ አድርጉ አይክበሩ ወይ ሥልጣን አይያዙ እያልኩ አይደለም - የምለው የአሁኖቹ በደምብ የምናውቃቸው ወያኔ-ትግሬዎች ትልቁን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ልጓም እስከጨበጡ ድረስ እመኑኝ እውነተኛ ሰላም አይኖረንም፡፡ ይሄው አሁን እንኳን ከሌላው ጎሣ የወጣ ጠ/ሚኒስትር በአጭር ጊዜ ውስጥ "ለምን ይህን ያህል ተቀባይነት አገኘ? ለምንስ ስሙ በዚህን ያህል ፍጥነት በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ገነነ?" ብለው ነው ሊበቀሉት የሚራወጡት፡፡ እንጂ አቢይ የበደላቸው ነገር ኖሮ አይደለም፤ እንዲያውም እነሱን ለማስደሰት በተጓዘው ርቀት ቂምንና ኩርፊያን ሳያተርፍበት እንዳልቀረ እጠራጠራለሁ፡፡ እነሱ ግን ምን ጊዜም የበሉበትን ወጪት ሰባሪ እንደመሆናቸው  በሚታወቁበት የዘወትር መፈክራቸው "ሁሉንም አለዚያ ምንም!" እንዳሉ አሁን ድረስ ደርቀው አሉ፡፡  ይህ የሰሞኑ ገበያን የማስወደድ ተግባራቸው ተራ ምቀኝነትና "ይህ በስውዓት ተጋዳላዮቻችን ያገኘነው ሥልጣን ለምን ወደሌላ ብሔር ገባ?" ከሚል ድንቁርና የመነጨ ነው፡፡ በውነቱ ከሆነ ገበያን የሚያንር ምንም የተለዬ ምክንያት የተፈጠረ አይመስለኝም፡፡ እነሱው ናቸው እየበጠበጡን ያሉት፡፡ ሁሉንም ነገር አንድ ወገን ሲቆጣጠረው ደግሞ ሊፈጠር የሚችለውን ጣጣ እያየን ስለሆነ ለወደፊቱ ብዙ መጠንቀቅ የሚገባን ነገር ሳይኖር አይቀርም፡፡

ገበያውን እሳት አድርገውታል፡፡ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ሁሉ ዋጋቸው የማይቀመስ ሆኗል፡፡ ገበያ ወጥቶ አብዶ የማይመለስ ዜጋ የለም፡፡ ጨርቅም ብረትም ምንም ነገር ልግዛ ብትል ዋጋው ጦፏል፡፡ የዘይቱ፣ ስኳሩ፣ ቅቤው፣ ሥጋው፣ የሁሉም ዋጋ በዕጥፍ እያደገ ነው፡፡ ድሃ መኖር አልቻለም፡፡ በአንድ የገጠር ከተማ አንድ ኪሎ ስኳር ከ60 ብር እስከ 80 ብር ገብቷል ብላችሁ በተለይ ዲያስፖራዎች ልታምኑኝ አትችሉም፡፡ አዲስ አበባ ላይ የአንድ ኪሎ ፉርኖ ዱቄት ዋጋ 25 ብር ገደማ ነው፡፡ አንድ ኪሎ ሙዝ 25 ብር ነው፡፡ አንድ ኪሎ ፓፓየ 25 ብር ነው፡፡ አንድ ሦስተኛ ሊትር ዘይት 25 ብር ነው፡፡ አንዷት ብልቃጥ የፊት አምባር ጭቃ 25 ብር ናት፡፡ ከአፈርና ግርድ ውጪ ጄሶ ያልገባበት አንድ ኩንታል ነጭ ጤፍ 3000 ብርን ሊነካ ጥቂት ብሮች ይቀሩታል፡፡ በአሁኑ ዘመን አንድ ኩንታል ጤፍ ለማስፈጨት ለአባሜንቶ የሚከፈለው ገንዘብ በዱሮው ዘመን ሁለት ኩንታል ማኛ ጤፍ ይሸምት በር፡፡ አስቡት - የ600 ብር ደሞዝተኛም አለ፡፡ እንዴት ይኑር? በምን ይኑር? የት ይኑር? በምን ይጓጓዝ? በምኑ ይታከም? ልጆቹን የትና እንዴት ያስተምር? ግራ እሚያጋባ ጊዜ እኮ ነው! መተሳሰብም ጠፋ፡፡ መንግሥት የሚባል የዜጎች አባትም የለም፡፡ ለዜጋው ማን ያስብለት? ለዕውር አሞራ እንኳ ወፎች አስበውለት ርቦት አፉን ሲከፍት የሚበላው ነገር ይጥሉለታል፡፡ ሰው ግን የባሰበት ዐውሬ ሆነና ማጉረሱ ቀርቶ ድሃ የጎረሰውን ከአፉ አውጥቶ የሚበላ አጋሰስ ተፈጠረ፡፡ "መጥኔ ለወለደሽ!" አሉ እማ ትርፌ - በሾርኒ ግን "ያገባሽስ ይፈታሻል!" ማለታቸውን ያስታውሷል፡፡  ችግሩ ወደኛ ሲመጣ ነው፤ እኛስ ማን አለን? ሲአይኤ በጠማማ ቀን ካጋባን ወያኔ ማን ያፋታን? መጥኔ እነዚህን ጉዶች ለወለደ!

**ምን እናድርግ? መፍትሔው የሚመስለኝ...**

1. ጤናማ አስተሳሰብ ያላችሁ የገዢው መደብ አባላት ነጋዴዎችና የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ይህ ጊዜ እንደሚያልፍና ደህና ዘመንም እንደሚመጣ በመገንዘብ ከዚህ ዓይነቱ ዘረኝነትን መሠረት ያደረገ አስነዋሪ ድርጊት ተቆጠቡ፡፡ የምትሠሩት ጠያፍ ሥራ በታሪክ ተመዝግቦ ነገ በትውልዶች መካከል ቁርሾ የሚያስቀምጥና የሚያቆራቁስ በመሆኑ በአስቸኳይ ከዚህ ድርጊት ታቀቡ፡፡
2. "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል" እንደሚባለው ሌሎች ነጋዴዎች ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለመክበር ያላችሁን ፍላጎት ገታ አድርጋችሁ ለሕዝባችሁ አስቡ፡፡  የሚያልፍ ቀን የማያልፍ የኀሊና ጠባሳ አስቀምጦባችሁ እንዳያልፍ እናንተም ብትጠነቀቁ ይበጃችኋል፡፡ ተንደላቆ መኖር የሚቻለው ሀገርና ሕዝብ ሲኖሩ ነውና የተናጠል ብልጽግናችሁ ከብልግና  ተለይቶ ስለማይታይ በቶሎ ወደየኅሊናችሁ ተመለሱ፡፡ እርግጥ ነው - ሀብት አይጠገብም፤ ገንዘብን በቃኝ ማለትም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁንና የሥጋን ፈተና ቻል አድርጋችሁ ለወገናችሁ አስቡ፡፡
3. ገበያተኛው ሕዝብ ከወያኔዎችና ከአሽቃባጮቻቸው  መግዛቱን ትቶ ለሀገር ቅን ከሚያስቡና በወያኔ ከተጨቆኑ ነጋዴዎች ጋር ይገበያይ፡፡ በወያኔዎች የንግድ ማዕከላት መገበያየቱንም ያቁም፡፡ አንዱና ትልቁ ኃይላቸው ገንዘብ ነው፡፡ በራሳችን ገንዘብ እንዳይጎዱን ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ መሞቻ ዱላውን ገዝቶ የሚሰጥ በራሱ የፈረደ ነው፡፡
4. **እየሆነ ያለው ጠ/ሚኒስትሩን በሕዝብ ለማስጠላት መሆኑን ገበያተኞች ተረድተን** በወያኔ ወለድ የሸቀጦች ዋጋ መናር ሳንበሳጭና ለጠ/ሚኒስትሩ ድጋፋችንንም ሳንነፍግ የወቅቱን ፖለቲካ ንፋስ መከታተል ይገባናል፡፡ የሚገዛው ነገር ቢወደድብን ጊዜ የሚሰጥ ከሆነ ለጊዜው አለመግዛት፡፡ በግድ የሚያስፈልገን ከሆነ ግን መጠኑን እየቀነስን መግዛት ወይም ከቦታ ቦታ አማርጠን በተሻለ ዋጋ ለማግኘት መሞከር፡፡ ለምሣሌ በፊት አሥር ኪሎ ወይም አሥር ሊትር አንድ ነገር እንጠቀም ከሆነ በግማሽ ወይም በሩብ በመቀነስ መጠቀምን መለማመድ - እንደዘይትና የመሳሰሉት የምግብ ሸቀጦች ላይ ይህ ዘዴ ሊያገለግል ይችላል፡፡
5. አንድ ነገር ይጠፋ ይሆናል በሚል አለመስገብገብ፡፡ ከጠፋም ይጥፋ፡፡ ከሞት የሚመልስ አይደለም፡፡ ምግብ እንኳን በቀን ሦስቴ የምንበላ ብንሆን በተቻለን መጠን ወደ ሁለትና አንድ መለወጥ፡፡ እንደሰማሁት በችግር ጊዜያት ስለሀገር ፍቅር ሲባል ብዙ መስዋዕትነትን መክፈል ያለና የነበረ ነው፡፡ ለምሣሌ እስራኤላውያን ለስድስት ወራት ያህል ደሞዝ ሳይሆን ራሽን እየወሰዱ አንድ የችግር ወቅት አልፈዋል አሉ፡፡ ከነሱ ብዙ መማር እንችላለን፡፡ ለነዚህ  የአእምሮ ድኩማን ከተንበረከክን ቋንጃችንን እየቆረጡ የጥንቶቹን የግንደ በረት ባርያዎች እንደሚያደርጉን አንጠራጠር፡፡ ስለዚህ ለሸቀጥ ብለን ይህን ልጅ እንዳንጠላ እንጠንቀቅ፡፡ በጭብጥ ምሥር  ወንድሙን አሳልፎ እንደሸጠው ምሥኪን ርሀብተኛ እንዳንሆንና ለሆዳችን እንዳንገዛ የዜግነቴን ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡
6. የመንግሥት ሠራተኞች የሆናችሁ ኃላፊነታችሁን በአግባቡ ተወጡ፡፡ ለዛሬ የወያኔ ተልካሻ ዓላማ ብላች የነገ ዕድላችሁን አታባክኑ፡፡ አነሰም በዛ ደመወዝ የሚከፈላችሁ ከዚህ ባዶ እግሩን ከሚሄድ ምሥኪንና ድሃ ሕዝብ ተሰብስቦ ነውና በሕዝብ አትጫወቱ፡፡ ሕዝብን አክብሩ፡፡ እግዚአብሔርንም ፍሩ፡፡ በእንጀራችሁም አታላግጡ፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ገንዘቡንም ሆነ የዕቃ ግብይቱን እነሱው ስለያዙት ማንኛችንንም የመጉዳት አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ከነቃንባቸው ግን ምንም አያመጡም፡፡ ለሚያልፍ ነገር አንማረርላቸው፡፡ እንዲያውም ደስ ይበለን፡፡ ስንበሳጭላቸው ደስታውን አይችሉትም፡፡ ደግሞም ይህን ዕኩይ ሥራቸውን ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ እናጋልጥ፡፡ ሕዝቡ ይወቀው፡፡ ጸሐፍትና አክቲቪስቶችም በዚህ ነገር ዙሪያ ዝመቱ፤ ሕዝቡን አንቁ፡፡ "አሁን ለጊዜው እኔን ካልቸገረኝ ምን አገባኝ?" አንበል፡፡ ያንዱ ችግር የሌላውም እንደሆነያህል አንዳችን ለአንዳችን እንተሳሰብ፤ እንተዛዘን፡፡ ስለዚህ ሕዝቡን ስለተጨባጩ የሀገራችን ሁኔታ በግልጽ እየነገርነው ጠላትና ወዳጁን ይለይ፡፡ ከዚህ በተረፈ "ሰማይና ምድርም ያልፋሉ - እንኳንስ ጊዜ ወለድ ችግር" በማለት ልሰናበት፡፡

ለገምቢ አስተያየት - mz23602@gmail.com